Haile Selassie I - Harar Military Academy North America
ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሐረር ጦር አካዳሚ ሰሜን አሜሪካ

# ሜይ 03 ቀን 2026 (ግንቦት 25 ቀን 2018 ዓ.ም) የተካሄደ አሉምናይ ማህበራችን መደበኛ ስብሰባ

## (Highlights of May 03, 2026  Bimonthly Meeting)

የቀዳማዊ ሐይለስላሴ/ሐረር ጦር አካዳሚ ምሩቃን ማህበር በሰሜን አሜሪካ በሁለት ወር አንድ ጊዜ የሚያካሄደውን መደበኛ ስብሰባ ግንቦት 25 ቀን *20218* ዓ.ም *(May 03, 2026) "6120 Manchester Lakes Drive, Alexandria,VA 22310"* በሚገኘው መዝናኛ ማእከል አዳራሽ አካሂዷል።

የእለቱን መስተንግዶ ያዘጋጁት ኮሎኔል ክንድያ ከበደና ባለቤታቸው ወይዘሮ ዘለቀ ተገኑ ናቸው።

 

የስብሰባው ሰዓት፦ከ**1:00-5:00** ፒ.ኤም ነበር። ከ**1:00-2:00** የአባላት መድረሻ ጊዜ ሆኖ ከ**2:00-3:00** ፒ.ኤም የምሳና ከ**3:00-5:00** ሰዓት ደግሞ የውይትና ማህበራዊ ጊዜ ነበር።

በስብሰባ የተገኙ አባላት፦ በስብሰባው ***35*** አባላትና ***25*** የቤተሰብ አባላት በድምሩ 60 ሰዎች ተገኝተዋል።

ከምሳ በፊት ለማህበሩ አባላት “የእንኩዋን ደህና መጣችሁ” ሰላምታ ከቀረበ በኋላ የእንግዶች ትውውቅ ተደርጓል።

 

በእለቱ የተገኙት እንግዶች፦ ሻለቃ ዶ/ር ግርማ ተፈራ (18ኛ ኮርስ)፤ ኮሎኔል መኮንን ረጋሳ (18ኛ ኮርስ)፤ እ/መ እስጢፋኖስ አሸብር (18ኛ ኮርስ) ነበሩ።

 


ከእንግዶች ትውውቅ ቀጥሎ በቅርቡ ከዚህ ዓለም በሞት ለተለዩት የአካዳሚው ምሩቅና የ21ኛ ኮርስ አባል ሻለቃ/ዶ/ር አበራ ሁንዴ የአንድ ደቂቃ ሂሊና ጸሎት ተደርጓል። ከዚያም የማህበራችን ሊ/መንበር ኮሎኔል ጋተው ተፈሪ የእለቱን መስተንግዶ ለአዘጋጁት ኮሎኔል ክንድያ ከበደና ባለቤታቸው ወይዘሮ ዘለቃ ተገኑ ምስጋና አቅርበው አባላት ምሳ ተስተናግደዋል።

ከ**3፡00-5፡00** ፒ.ኤም በነበረው ፕሮግራም በአንድ አጀንዳ ጉዳይ ላይ ውይይት ተካሂዷል። አስቀድሞ ማርች ***29*** ቀን ***2026*** የተከሄደው ሰብሰብ ቃለ-ጉባኤ በንባብ

ተሰምቶ አባላት በሙሉ ድምጽ አጽድቀውታል። ከቃለ-ጉባኤው ጋር ተያይዞ በተለያዩ ኮሚቴዎች ውስጥ የተመረጡት አባላት ስለ ስራቸው ሂደት በየጊዜው ወቅታዊ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ማሳሰቢያ ተሰጥቷል።

በእለቱ ትልቅ ትኩርት የተሰጠው ጉዳይ "ቀዳማዊ ሃይለስላሴ/ሐረር ጦር አካዳሚ የተመሰረተበት **68**ኛ ዓመት" መታሰቢያ ቀን ነበር።

የጦር አካዳሚ ማህበር አባላት ቀዳማዊ ሃይለስላሴ/ሐረር አካዳሚ የተመሰረተበት ቀን በየዓመቱ ሚያዚያ ***27*** ቀን (ሜይ ***05***) በመታሰቢያነት እንዲከበር በ2025 ዓ.ም በወሰኑት መሰረት በሰሜን አሜሪካ የሚኖሩ የቀዳማዊ ሃይለስላሴ/ሐረር ጦር አካዳሚ ምሩቃን ማህበር ቀኑን በሁለት ዋና ጉዳዮች አስቧል፦

1. በ***2025/26*** ዓ.ም ከመካከላችን በሞት የተለዩትን የጦር አካዳሚ ምሩቃን አስበ ውሏል። በ2025/26 ከዚህ ዓለም በሞት ለተለዩት የአካዳሚ ምሩቃን፦ ሻለቃ ተሾመ ሸንቁጤ (17ኛ ኮርስ)፤ ኮሎኔል መለስ ወልደዮሐንስ (6ኛ ኮርስ)፤ ሻለቃ ወርቅነህ መኮንን (21ኛ ኦርስ)፤ መ/አለቃ ዳምጤ ይልማ (16ኛ ኮርስ)፤ ሻለቃ ሙሉጌታ ከበደ (3ኛ ኮርስ) እና ሻለቃ/ዶ/ር አበራ ሁንዴ (21ኛ ኮርስ) የአንድ ደቂቃ ሂሊና ጸሎት ተደርጎላቸዋል።

2. ሻለቃ ሃይለማርያም አባይና ሻለቃ ኢያሱ አያልቅበት (ሁለቱም አካዳሚ 1ኛ ኮርስ ምሩቃን) እለቱን በማስመልከት ስለ አካዳሚው ምስረታ ታሪክ የቃል ምስክርነት አሰምተዋል።



ሻለቃ ሃይለ ማርያም አባይ



ሻለቃ ኢያሱ አያልቅበት

## የሻለቃ ሃይለማርያም አባይ ሕይወት ጉዞ ምስክርነት

"ቀዳማዊ ሃይለስላሴ/ሐረር ጦር አካዳሚ የተመሰረተበትን **68**ኛ ዓመት መታሰቢያ ቀን አስመልክቶ ሻለቃ ሃይለማርያም አባይ (1ኛ ኮርስ አባል) ስለ ጦር አካዳሚው ምስረታና ስለ ግል ሕይወታቸው ልምዳቸውን እንዲያከፍሉ በተጠየቁት መሰረት ከአንደኛ እስከ 21ኛ ኮርስ ያሉ የአካዳሚው ምሩቃንና የቤተሰብ አባላት በተገኙበት ስብሰባ ላይ ተገኝተው ስለ ጦር አካዳሚው አጀማመር ታሪክና ስለ ግል ሕይወታቸው ልምዳቸውን አካፍለዋል። ከተወለዱበት አድዋ ጀምሮ ዛሬ እስከ ሚኖሩበት አሜሪካ ድረስ የተጓዙበትን የ88 ዓመታት የሕይወት ጉዞ፤ በኢትዮጵያና በውጭ አገር ስላሳለፉት ዘመንና ስላበረከቱት አገልግሎት በሰፊው አጫውተውናል። ሻለቃ ሃይለማርያም የተወለዱት በትግራይ ክፍለ ሀገር አድዋ ከተማ እንደሆነና እድሜአቸው ለትምህርት እንደ ደረሰም አድዋ ከተማ ውስጥ ቄስ ት/ቤትና ንግስት ሳባ ት/ቤት መደበኛ ትምህርት እንደ ተመሩ ተናግረዋል። ቀጥሎም የንጉሱ ባለሟል የነበሩት አባታቸው ደጃዝማች አባይ ለስራ ወደ አዲስ አበባ ሲዛወሩ አራት ልጆቻቸውን ወደ አዲስ አበባ በማስመጣት እርሳቸውንና ታላቅ ወንድማቸውን ቃለ-ክርስቶስ አባይን ተፈሪ መኮንን ት/ቤት፤ ሁለቱን እህቶቻቸውን ደግሞ እቴጌ መነን ት/ቤት እንዳስገቧቸው ገልጸዋል።

ተፈሪ መኮንን ት/ቤት ውስጥ ትምህርታቸውን በጥሩ ሁኔታ እያተከታተሉ እያሉ በት/ቤቱ ውስጥ በሁለት ሃይማኖቶች (ኦርቶዶክስና ጀስዊት) መካከል በተፈጠረው

ልዩነት ምክንያት ተማሪዎች አድማ በማድረጋቸው መሪዎቹ ተለይተው ለቅጣት ሲዳረጉ እርሳቸው በአድማ ውስጥ አለመኖራቸውን ቢናገሩም ሰሚ አጥተው በሃሰት እንደ ተወነጀሉና ከአድመኞቹ ጋር ንጉሱ ዘንድ እንደ ቀረበው ያልጠበቁት ውሳኔ እንደ ተወሰነባቸው በትዝታ አስታውሰዋል። ንጉሱ በሰጡት ውሳኔም የተወሰኑት ተማሪዎች እንዲታሰሩ ሲደረግ እርሳቸውና ሌሎች ደግሞ ከተፈሪ መኮንን አዳሪ ት/ቤት ወጥተው ወደ ወላጆቻቸው ቤት እንዲመለሱ ተደርጎ ነበር። በዚህ ምክንያትም ያለ ፍላጎታቸው ተፈሪ መኮንን ት/ቤትን ለቅቀው መድሃነዓለም ት/ቤት ገቡ። ወንድማቸው ቃለ-ክርስቶስ አባይ ከተፈሪ መኮንን ት/ቤት ለክብር ዘበኛ አንደኛ ኮርስ እጩ መኮንንነት ተመልምለው ክቡር ዘበኛ አካዳሚ ገቡ። ከክቡር ዘበኛ አካዳሚ በም/መ/አለቃ ማእረግ ተመርቀው እዚያው ክብር ዘበኛ ጦር ክፍል ውስጥ እስከ ኮሎኔል ማእረግ ደርሰው አገራቸውን በውትድርና እናዳገለገሉ ገልጸዋል።

ሻለቃ ሃይለማርያም መድሃነዓለም ት/ቤት እያሉ የአየር ሃይል ባልደረቦች ተማሪዎችን ለመመልመል ወደ ት/ቤታቸው በመጡበት አጋጣሚ የአየር ሃይል መግቢያ ፈተና ተፈትነው ካለፉ በኋላ ከሶስት ጓደኞቻችው ጋር አየር ሃይል ገቡ። አየር ሃይል ሲገቡ ፍላጎታቸው አውሮፕላን አብራሪ ለመሆን ነበር። ነገር ግን የተመኙት የአውሮፕላን በረራ ስላልተሳካላቸው አየር ሃይልን ለቀው አየር መንገድ ውስጥ የትኬት ኤጀንት ሆነው ተቀጠሩ። የአየር መንገድ ስራቸውን የጀመሩት በአዲስ አበባ ውስጥ ቢሆንም ስድስት ወር እንደሰሩ ወደ አስመራ ተዛወሩ። አስመራ ለተወሰኑ ዓመታት ከሰሩ በኋላ እንደገና ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው ፒያስ በሚገኘው አየር መንገድ ትኬት ቢሮ ስራ ጀመሩ። አጋጣሚውን ተጠቅመው ቀን ቀን ስራቸውን እየሰሩ የማታ ትምህርታችውን በመማር 12ኛ ክፍል ከጨረሱ በኋላ የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ መልቀቂያ ፈተና ተፈትነው በጥሩ ውጤት አለፉ። የአስራ ሁለተኛ ክፍል ብሔራዊ መልቀቂያ ፈተና (ማትሪክ) ካለፉ በኋላ ስራቸውን ለቅቀው ከፍተኛ ትምህርት ለመቀጠል ወሰኑ። ፍላጎታቸው ገበሬ ለመሆን ስለ ነበር በቀጥታ ወደ ዓለምማያ ኮሌጅ ሄደው የግብርና ትምህርት መከታተል ጀመሩ።

ዓለምማያ ኮሌጅ ትምህርታቸውን መከታተል ላይ እያሉ ከዓለምማያ በቅርብ ርቀት ላይ አዲስ የተቋቋመው ጦር አካዳሚ እጩ መኮንኖችን ለመቅጠር በኮሌጁ ውስጥ የለጠፈውን ማስታወቂያ ካነበቡ በኋላ ልባቸው ወደ ውትድርና አዘነበለ። ከዚያም የኮሌጅ ትምህርታቸውን አቋርጠው አካዳሚ ለመግባት ወሰኑ። ጓዳኞቻቸው ከነበሩት ደሳለኝ አበበ (በኋላ ብ/ጄኔራ)፤ ማሞ መዘመር (በኋላ መ/አለቃ) እና ከሌሎች ሶስት ጓደኞቻችው ጋር አምስት ሆነው በፈቃደኝነት ከተመዘገቡ በኋላ ጦር አካዳሚ ለመግባት ወደ ሐረር ሄዱ። አካዳሚ እንደ ደረሱም ከአዲስ አበባ የኮሌጅ ትምህርታቸውን አቋርጠቅ በግዴታ ወደ አካዳሚው ከተላኩት 35 ተማሪዎች ጋር ተገናኙ። እነዚህ የተሰባሰቡት አርባ (40) የ1ኛ ኮርስ እጩ መኮንኖች የመጀመሪያ ዓመት ትምህርታቸውን የጀመሩት ሚያዚያ **27** ቀን **1950** ዓ.ም ነበር። ሻለቃ

ሃይለማርያም የአካዳሚ ትምህርታቸውን እንደ ጀመሩ ከካዴት አዛዥ መኮንን ጋር በነበረባቸው የግል ችግር ምክንያት ስልጠናውን አቋርጠው ለመውጣት ሙከራ አድርገው ነበር። ነገር ግን እየቆዩ ሲሄዱ መግባባት ስለ ተፈጠረና የበለጠ ተወዳጅነትንም እያገኙ ስለሄዱ "ካዴት አጁታንት" (Cadet Adjutant ) እስከ መሆን ደርሰው ነበር። በአካዳሚው ለሶስት ዓመታት የሚሰጠውን ስልጠና በጥሩ ሁኔታ ከጨረሱ በኋላ ከኮርስ ጓደኞቻቸው ጋር መስከረም 21 ቀን 1953 ዓ.ም በም/መ/አለቃ ማእረግ ለመመረቅ በቅተዋል።

ከአዲስ አበባ ኮሌጅችና ከዓለምማያ ግብርና ኮሌጅ ተመልምለው አካዳሚ ለገቡት የአንደኛ ኮርስ እጩ መኮንኖች ንጉሱ አካዳሚውን ሲከፍቱ ባደረጉት ንግግር "ከኮሌጅ ከሚመረቁ ጓደኞቻችሁ አናሳንሳችሁም" የሚል ቃል ገብተው ነበር። ይህም ከአዲስ አበባ ኮሌጅ ለሚመረቁ ተማሪዎች የሚከፈለውን 450 ብር ደመወዝ ለአካዳሚ ምሩቃንም እንደ ሚከፈላቸው ነበር። ነገር ግን የተገባላቸው ቃል ባለመፈጸሙ ምክንያት ቅሬታን አስከትሎ አቤቱታ እስከ ንጉሱ ቀርቦ ነበር። ሆኖም ምንም የረባ መልስ ሳይሰጥ ከአካዳሚ ሲመረቁ የተከፈላቸው 125 ብር የም/መ/አለቃ ደመወዝና 90 ብር የድፕሎማ አበል በድምሩ 215 ብር ብቻ እንደ ነበር በሃዘኔታ ገልጸዋል።

ከአካዳሚ እንደተመረቁ ሻለቃ ሃይለማርያም የተመደቡት ክቡር ዘበኛ ጦር ክፍል ውስጥ ነበር። ክቡር ዘበኛ ውስጥ ስራ እንደ ጀመሩ በ1953 ዓ.ም በተሞከረው መፈንቅለ መንግስት ምክንያት ለእስር ተዳርገው እንደ ነበር ገልጸዋል። እርሳቸው መፈንቅለ መንግስት መኖሩን እንኳን ያወቁት ደመወዛቸውን ለመውሰድ መርካቶ ንግድ ባንክ በሄዱበት አጋጣሚ ነበር። ነገር ግን ምንም ዓይነት ተሳትፎ ሳይኖራቸው ማሿለኪያ አከባቢ በሚገኘው 4ኛ ክፍለ ጦር መምሪያ ውስጥ ከበርካታ መኮንኖች ጋር መታሰራቸውን ገልጸዋል። ደግነቱ እንደ ሌሎቹ እስር ቤት ውስጥ ብዙ ሳይቆዩ ሌ/ጀኔራል ሃይሌ ባይከዳኝ ከጦር አካዳሚ አዛዥ ጋር ተነጋግረው ወደ አካዳሚ እንደላኳቸው ተናግረዋል። አካዳሚ ውስጥ ጥቂት ጊዜ እንደቆዩ የከፍተኛ ትምህርት እድል አግኝተው ከአራት ጓደኞቻቸው ጋር ለምህንድስና ትምህርት ወደ ህንድ አገር ሄዱ። ከእነሱ በፊት እነ ጥበበ መንክር ምህንድስና ተምረው እንደተመለሱና እነሱ ሁለተኛ ዙር መሆናቸውን ገልጸዋል።

ህንድ አገር ለትምህርት የተላኩት አምስቱ መኮንኖች ትምህርታቸውን ጨርሰው እንደ ተመለሱ "ጃንሆይ" (ቀዳማዊ ሃይለስላሴ) ዘንድ ቀርበው የተፈጠረውን አጋጣሚ በትዝታ አጫውተዋል። ንጉሱ ዘንድ ሲቀርቡ የምድር ጦር አዛዥ ሜ/ጀኔራል ሺፈራውና የመከላከያ ሚኒስቴር ችፍ ኦፍ ስታፍ ሌ/ጀነራል ከበደ ገብሬ አጠገባቸው እንደ ነበሩ ያስታውሳሉ። አምስቱም መኮንኖች ንጉሱ ዘንድ ቀርበው ተሰልፈው እንደቆሙ "የጃንሆይ ውሻ" ድንገት መጥታ ሻለቃ ሃይለማርያም እግር ስር እንደ ገባችና የውሻዋ ሁኔታ ትኩረታቸውን ስለ ሳበች ይመስላል! ያኔ ንጉሱ ፊታቸውን ወደ

ሻለቃ ሃይለማርያም አዙሮው "ምን ተምራችሁ መጣችሁ?" ብለው እንደ ጠየቁና እርሳቸውም "ጃንሆይ! ምንም አልተማርንም!" መንግስት ብዙ ውጪ አወጥቶ የረባ ትምህርት ሳንማር ነው የተመለስነው" ብለው ሲመልሱ ንጉሱ በጣም ተገርመው "እንዴት? ታዲያ ምንድነው የምትለው? መሐንዲሶች አይደለንም እንደገና ወደ ህንድ ተመልሰን እንማር ነው የምትለው"? አሉ። በዚያን ጊዜ "አረ! አይደለም ጃንሆይ እዚሁ ኢትዮጵያ ውስጥ ኮሌጅ ገብተን እንድንማር ይፈቀድልን!" በማለት መልስ ሰጡ። ከዚያም ጃንሆይ ወደ ጄኔራሎቹ ዞሮው "እንግዲያውስ እንዲማሩ ይፈቀድላቸው" አሉ። ጄኔራል ሺፈራው ወዲያው "ድጋሚ ለትምህርት ለመላክ በተማሩት ትምህርት ቢያንስ ሁለት ዓመት ማገልገል አለባቸው" በማለት ተቃውሟቸውን አሰሙ። በዚያን ጊዜ ንጉሱ "ታዲያ አልተምርንም እያለ ተመልሰህ ሂድ ትለዋለህ? እኔ ፈቅጄላቸዋለሁ!" አሉ።

ከጃንሆይ ዘንድ እንደ ተመለሱም አምስቱ መኮንኖች ኮሌጅ ገብተው እንዲማሩ ተፈቅዶላቸው ሕንጻ ኮሌጅ ለምዝገባ ሄዱ። አራቱ ጓደኞቻቸው የምህንድስና ትምህርት ለመማር ሲመዘገቡ ሻለቃ ሃይለማርያም ግን የምህንድስና ትምህርት መማር እንደ ማይፈልጉ ተናገሩ። ሕንጻ ኮሌጅ የሚያስተምረው ምህንድስና ትምህርት ብቻ ስለሆነ ሌላ ትምህርት መማር ከፈለግህ ወደ አራት ኪሎ ሂድ! ብለው መከሯቸው። እርሳቸውም አራት ኪሎ ሄደው የቀድሞ ተፈሪ መኮንን ጓዳኛቸው የነበሩትን ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያምን አግኝተው ምን ማድረግ እንደ ሚገባቸው ምክር ጠየቁ። ፕሮፌሰር መስፍንም ወደ ሶሻል ሳይንስ ኮሌጅ ሄደው ፕርፎፌሰር ስዩም ገብረስላሴን እንዲያናገሩ መከሯቸው። በዚያ መሰረት ሶሻል ሳይንስ ፋኩልቲ ሄደው ፕሮፌሰር ስዩምን አነጋገሩ። ፕሮፌሰር ስዩም ያለ ምንም ችግር ተቀብለው ካነጋገሩ በኋላ በሶሻል ሳይንስ ዲፓርትሜንት ተመዝግበው ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ፈቀዱላቸው። ትምህርታቸውን ሲጀምሩም አካዳሚ ውስጥ የተማሩት ትምህርት ተቆጥሮላቸው ከሶስተኛ ዓመት እንዲጀምሩ ተፈቀደላቸው። በዚህ ምክንያት ትምህርታቸውን በአጭር ጊዜ ጨርሰው በ"ፓብሊክ አድሚንስትሬሽ ቢ.ኤ" ድግሪ ተመረቁ። እስር የአካዳሚ ምሩቃን በየዓመቱ ዩኒቨርሲቲ ገብተው እንዲማሩ የተፈቀደው ከዚያ በኋላ ነበር። በዚህም ሻለቃ ሃይለማርያም የመጀመሪያው ፈር-ቀዳጅ" መሆናቸውን በትውስታ ተናግረዋል።

ሻለቃ ሃይለማርያም ከአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ተመርቀው ወደ መከላከያ ተመልሰው ሪፖርት ሲያደርጉ ችግር ገጠሟቸው እንደነበር አልሸሸጉም። የተላኩት ምህንድስና እንዲማሩ ሆኖ ሳለ እርሳቸው ግን ተምረው የተመለሱት የአድሚንስትሬሽን ሙያ መሆኑን ለመከላከያ ሚኒስቴር ሪፖርት ሲያደርጉ ሃላፊው መኮንን "ማን አድሚንስትሬሽን እንድትማር ፈቀደልህ"? በማለት እንደተቆጡና እንደ ገሰጿቸው ተናግረዋል። ሆኖም ጉዳዩ ለመከላከያ ችፍ ኦፍ ስታፍ ሌ/ጄኔራ ኢስያስ ገብርስላሴ ቀርቦ የእርሳቸው ኤ.ዲ.ሲ ሆነው እንዲሰሩ ስለ አዘዙ ልዩ ረዳታቸው ሆነው

መስራታቸውን ገልጸዋል። ጄኔራል ኢሳያስ የሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ ሆነው በመሸም መከላከያ ሚኒስቴርን ሲለቁ በምትካቸው የመከላከያ ችፍ ኦፍ ስታፍ ሆነው ለተሾሙት ለሌ/ጄኔራል እያሱ መንገሻ "ይህ መኮንን እንዳያመልጥህ" ብለው ስለ ተናገሩ ጄኔራል እያሱም በኤ.ዲ.ሲ ስራቸው እንዲቀጥሉ ስላደረጉ መከላከያን እስከ ለቀቁበት ጊዜ ድረስ በልዩ ረዳትነት ሰርተዋል።

መከላከያ ውስጥ እየሰሩ እንደገና ሌላ የትምህርት እድል አግኝተው ውጭ አገር ሄደው የድህረ ምርቃ ትምህርት ተከታትለው በፓብሊክ አድሚንስትሬሽን ማስትሬት ድግሪ አግኝተዋል። ከውጭ አገር ከተመለሱ በኋላ በቀዳማዊ ሃይለስላሴ ትእዛዝ በወለጋ ጠቅላይ ግዛት የአሶሳ አውራጃ አስተዳዳሪ ሆነው በመሸም አገራቸውን አገልግለዋል። የአሶሳ አውራጃ አስተዳዳሪ ሆነው ባገለገሉበት ወቅት ጉቦኝነትንና ብልሹ አሰራርን አስወግደው ፍትሕና ርትህ በማስፈን አውራጃውን በልማት ለማሳደግ ባደረጉት ጥረት ከፍተኛ ተግዳሮቶች አጋጣሚቸው እንደነበረ ገልጸዋል። በተለይም እጅግ ተንሰራፍቶ የነበረውን የጉቦ ስርዓት ለማጥፋት በወሰዱት ጠበቅ ያለ እርምጃ ከባድ ተቃውሞ እንደ ገጠማቸውና እርሳቸውም ሳያውቁ በፈጸሙት ስህተት የፈለጉትን ለውጥ ማምጣት እንዳልቻሉ በጸጸት ተናግረዋል።

ከአሶሳ አውራጃ አስተዳዳሪነት በኋላ በአገር አስተዳደር ሚኒስቴር የአስተዳደር መምሪያ ሃላፊ ሆነው ሰርተዋል። አገር አስተዳደር እያሉ የመንግስት ለውጥ ተደርጎ ጊዚያዊ ወታደራዊ አስተዳደር መንግስት (ደርግ) ስልጣን ከያዘ በኋላ ደግሞ የቡናና ሻይ ልማት ሚንስቴር ቋሚ ተጠሪ ሆነው በከፍተኛ ሃላፍነት አገራቸውን አገልግለዋል። ቡናና ሻይ ልማት ሚኒስቴር ውስጥ እየሰሩ በነበሩበት ወቅት ከምንስትሩ ደምሰው ካሳዬ ጋር በስራ መግባባት ስላልቻሉ ቡናና ሻይ ልማት ሚንስቴርን ለመልቀቅ ተገደው ነበር። በዚህ ምክንያትም ቡናና ሻይ ልማት ሚኒስቴርን ለቅቀው ካሜሩን አገር በሚገኘው "ፓን አፍሪካን ኢንስቲቱት" ውስጥ ተቀጥረው ማገልገላቸውን ገልጸዋል። በፓን አፍሪካን ኢንስቲትዩት ውስጥ የተወሰኑ ዓመታት ከሰሩ በኋላ በወንድማቸው በላይ አባይ ጋባዥነት ከቤተሰባቸው ጋር ወደ አሜሪካ እንደመጡና ሌላ ስራ አግኝተው በጡረታ እስከ ተገለሉበት ቀን ድረስ መስራታቸውን ተናግረዋል። ሻለቃ ሃይለማርያም አባይ ከወይዘሮ ትሰሚ ሃይሌ ጋር ትዳር መስርተው ሁለት ወንዶችና ሶስት ሴቶች በድምሩ አምስት ልጆችን አፍርተዋል።

ሻለቃ ሃይለማርያም በረጅም ዓመታት የሕይወት ጉዞ ከልጅነታቸው ጀምሮ በግል ሕይወት፤ በትምህርት፤ በውትድርናና በሲቪል አገልግሎት ያበረከቱትን አስተዋጻኦ፤ ያጋጠሚቸውን ተግዳሮቶችና የስራ ልምድ ተሞክሮ በሰፊው አጫውተውናል። ሻለቃ ሃይለማርያም በተፈጥሮ የቀህ፤ ትሁት፤ ቅን አሳቢ፤ አሰባሳቢና ልዩነት ሳያደርጉ ሁሉንም ሰው የሚወዱ የፍቅር አባትና ተወዳጅ ወንድም ናቸው። በዚህ ወንድማዊ ፍቅርና ትህትና ጸባያቸው በሰሜን አሜሪካ የሚኖሩ የአካዳሚ ምሩቃንን በማሰባሰብ

የምሩቃን ማህበር እንዲመሰረት ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። ከምስረታው ጀምሮ አባላትን እንደ አንድ ቤተሰብ በማሰባሰብና ማህበሩን በሊ/መንበርነት በመምራት ለበርካታ ዓመታት አገልግለዋል። ስለ አካዳሚ ምሩቃንና ቤተሰብ ህብረትና አንድነት ብዙ የሚጨነቁ አንጋፋ ወንድም ናቸው። የአካዳሚ ምሩቅ በሙሉ በዚህ ማህበር ጥላ ስር ተሰባስቦ ቤተሰባዊ አንድነቱ ተጠናክሮ እንዲቀጥል የዘወትር ምኞታቸው ነው። የሰብሰባው ተሳታፊዎች ሻለቃ ሃይለማርያም ስላካፈሉት የሕይወት ተሞክሮ ምስጋናቸውን አቅርበው በቀሪው ዘመናቸው ለእርሳቸውና ለባለቤታቸው ትሰሜ ሃይሌ እንዲሁም ለውድ ልጆቻቸው እግዚአብሄር ጤናና ረጅም እድሜ እንዲሰጣቸው ምኞታቸውን ገልጸዋል።

ከሻለቃ ሃይለ ማርያም ቀጥሎ ስለ አካዳሚው ምስረታ ትውስታቸውን በተጨማሪ ያጋሩን ሻለቃ ኢያሱ አያልቅበት (1ኛ ኮርስ) ናቸው። ለአንደኛ ኮርስ የተመለመሉት አርባ (40) እጩ መኮንኖች ጦር አካዳሚ ከገቡ በኋላ አድዋ፤ ከረንና ጎንደር በተሰኙ ሶስት የእጩ መኮንኖች ሻምበሎች ተከፋፍለው ስልጠናቸውን እንደ ጀመሩ ተናግረዋል። በመጀመሪያ የነበረውን የአካዳሚ ዝግጅት በተመለከተም መኖሪያው፤ የምግብ አገልግሎትና የስልጠና ፋሲሊቲዎች በሙሉ የተሟሉ እንደነበር ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። ከአካዳሚው አዛዥ ጀምሮ በወታደራዊ ስልጠና ዘርፍ የተመደቡት መኮንኖች በሙሉ የህንድ ዜጎች እንደ ነበሩ ትውስታችውን አጋርተውናል። ስለ ሻምበሎቹ መጠሪያ ስም (አድዋ፤ ከረን፤ ጎንደር) የሚያውቁት ነገር እንዳለ እንድነግሩን ተጠይቀው ምክንያቱን በትክክል እንደ ማያውቁ ተናግረዋል። ሆኖም እጩ መኮንኖቹ በኮርስ ሳይሆን በሻምበሎች እንዲከፋፈሉ መደረጉ የበለጠ መቀራረብንና የውድድር መንፈስን ለመፍጠር የታሰበ ይመስላል።

በመጨረሻም ሁለቱ አንጋፋ የአካዳሚ በኩር ልጆች በመካከላችን ተገኝተው ልምዳቸውንና ትዝታቸውን ስላካፈሉ የማህበሩ አባላት ምስጋናቸውን አቅርበው ደስታቸውን በጭብጨባ ገልጸዋል። አካዳሚው ከተመሰረተበት ከ1ኛ ኮርስ እስከ 21ኛ ኮርስ ድረስ ያለውን የአንድነትና የፍቅር ሰንሰለት በማያያዝ ለቀሪው ትውልድ ማስተላለፍ በመቻላቸው እግዚአብሄርን አመስግነዋል፤ ለሁለቱም አንጋፋ ወንድሞች ረጅም እድሜና ጤና ተመኝተዋል።

በመጨረሻም የእለቱን በዓል በደማቅ ሁኔታ እንዲከበር እጅግ ጣፋጭ ምግብ ከመልካም መስተንግዶ ጋር ያዘጋጁትን ኮሎኔል ክንድያ፤ ወይዘሮ ዘለቃና መላው ቤተሰባቸውን በማመስገን ስብሰባው በ5:00 ሰዓት ተጠናቋል። የሚቀጥለው መስተንግዶ አዘጋጆች ሻምበል በዙ ወልደ ሚካኤልና ዶ/ር ሙሉ ከተተ መሆናቸውን በዚሁ ስብሰባ ተገልጿል።

የስብሰባ ተሳታፊዎች ፎቶግራፍ በከፊል




EXIT






